# ምዕራፍ ስድስት

## ነጥቦች፣ቀጥታ መስመሮች እና ቅርጾች(ምስሎች)

**ተግባር 6.1**

1. እርሳሳችሁን ተጠቅማችሁ ሁለት የተለያዩ ነጥቦችን አመልክቱ::
2. በመቀጠል እነዚህን ነጥቦች በፊደል ሰይሟቸው::
3. ማስመሪያ በመጠቀምና በማስመር ሁለቱን ነጥቦች አገናኟቸው:: ምን አገኛችሁ?

## 6.1 ማስመሪያን በመጠቀም ቀጥታ መስመሮችን መሣል

**ምሳሌ:-**




ሀ እና ለ ነጥቦች ናቸው::
ሁለቱን ነጥቦች ማስመሪያ ተጠቅመን ብናገናኛቸው የሚከተለውን ምስል እናገኛለን::




ስያሜውም ውስን ቀጥታ መስመር ሀለ ወይም ውስን ቀጥታ መስመር ለሀ ይባላል:: በፅሁፍ $\overline{\text{ሀለ}}$ በማለት እንገልፃለን::

1. ነጥቦች ምንጊዜም የሚሰየሙት በፊደላት ነው::


**ምሳሌ:-**

•ሀ ነጥብ ሀ

•ለ ነጥብ ለ

2. ቀጥታ መስመር የሚሰየመው በላዩ ላይ በሚገኙ ሁለት ነጥቦች ነው::

**ምሳሌ:-**





©MoE-FDRE Not to be rep


## 6.1.1 የነጥቦችና የመስመሮች ግንኙነት

**ተግባር 6.2**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ መልስ ስጡ፡፡




1. ሀ) ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ሀለ}}$ በነጥብ ______ላይ ያልፋል፡፡
   ለ) ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ሠረ}}$ በነጥብ _______ላይ ያልፋል፡፡
   ሐ) ነጥብ ‘መ’ የ _____እና______ መቋረጫ ነው፡፡
   መ) ነጥብ ______የመቋረጫ ነጥብ ተብሎ ይጠራል፡፡
   ሠ) ነጥብ መ በነጥብ _______እና _______ መካከል ይገኛል፡፡
   ረ) $\overleftrightarrow{\text{ሀለ}}$ በነጥብ _______ላይ ያልፋል፡፡
   ሸ) $\overleftrightarrow{\text{ሠረ}}$ በነጥብ _______ላይ ያልፋል፡፡
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡




ሀ. በነጥብ 'መ' ላይ ስንት መስመሮች አልፈዋል?
ለ. በነጥብ 'መ' ላይ ስንት መስመሮች ማለፍ ይችላሉ?
ሐ. በነጥብ 'መ' ላይ የሚያልፉትን ቀጥታ መስመሮች በሙሉ ዘርዝሩ፡፡

3. በተሰጡ ሁለት ነጥቦች ላይ ስንት ቀጥታ መስመር መስራት ትችላላችሁ?


•ሀ •ለ

4. የሚከተሉትን ነጥቦችና ቀጥታ መስመሮች ተመልከቱ፡፡

ሀ) ነጥብ 'ተ' ከቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{መነ}}$ ______ክፍል ይገኛል፡፡


ለ) ነጥብ 'ቀ' ደግሞ ከቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{መነ}}$ ______ ክፍል ይገኛል፡፡

ሐ) ነጥብ 'ረ' ቀጥታ መስመር ______ ላይ ይገኛል፡፡




## መልመጃ- 6ሀ

ከዚህ በታች የተቀመጡትን በመመልከት ከተራ ቁጥር 1 - 7 የተሰጡ ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡





1. ጨ ፣ ጀ፣ ________ ፣ ________ ፣ ________ እና ______ በመስመር ያልተገናኙ ነጥቦች ናቸው፡፡
2. ________ እና ________ውስን ቀጥታ መስመሮች ናቸው፡፡
3. ______፣______፣______እና______የውስን ቀጥታ መስመሮች ጫፍ ናቸው፡፡
4. _____፣ ______፣ _______እና ______ በቀጥታ መስመሮች ላይ የሚገኙ ነጥቦች ናቸው፡፡
5. ጨ እና ጀ ን በማገናኘት የምንሠራው ውስን ቀጥታ መስመር ________ ነው፡፡
6. ጀ እና ሠን በማገናኘት የምናገኘው ውስን ቀጥታ መስመር ______ ነው፡፡
7. ፈ እና ቀ ን በማገናኘት የምናገኘው ውስጥ ቀጥታ መስመር ______ ነው፡፡
8. ሁለት ነጥቦችን ወስዳችሁ በፊደሎች ካመለከታችሁ በኋላ በእነሱ ላይ የሚያልፍ ቀጥታ መስመር በማስመሪያ በመጠቀም ሳሉ፡፡ ቀጥታ መስመሩን ሰይሙ፡፡

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

9. በ8ኛ ጥያቄ ላይ ከሳላችሁት ቀጥታ መስመር ላይ በሚገኙ ሁለት ነጥቦች መካከል የሚገኘው ውስን ቀጥታ መስመር ምን ተብሎ ይጠራል? ውሰን ቀጥታ መስመሩን በፅሁፍ ምልክት ግለጹ፡፡

## መልመጃ- 6ለ

1. ከዚህ በታች የተሰጠውን ምስል በመጠቀም ጥያቄዎችን መልሱ፡፡





ምስል 1 ምስል 3

ሀ. ምስል 1 __________ ነው፡፡

ለ. ምስል 2 የመቋረጫ ነጥብ ______ ነው፡፡

ሐ. በምስል ሶስት ______ ነው፡፡

2. የሚከተሉትን ቀጥታ መስመሮችና ውስን ቀጥታ መሥመሮችን ሰይሙ፡፡




3. የሚከተሉትን ሳሉና ሰይሙ፡፡

ሀ. ውስን ቀጥታ መስመር $\overline{\text{ጨደ}}$ ሐ. ውስጥ ቀጥታ መስመር $\overline{\text{ሀለ}}$


ለ. ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ደቸ}}$ መ. ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ቀበ}}$

4. በነጥብ ረ ላይ የሚያቋርጡ ሁለት ቀጥታ መስመሮችን ሳሉና ሰይሙ፡፡

5. ሁለት የሚያቋርጡ ቀጥታ መስመሮችን ሳሉ፡፡ የሚያቆሙበትን ቦታ ቀ ብላችሁ ሰይሙ፡፡

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

6. የሚከተሉትን ውስን ቀጥታ መስመሮች ርዝመታቸውን አወዳድሩ::




ሀ. ከ $\overline{\text{ጨደ}}$ እና ከ $\overline{\text{ጠየ}}$ የቱ ይረዝማል?

ለ. ከ $\overline{\text{ጨደ}}$ እና ከ $\overline{\text{ገቸ}}$ የቱ ይረዝማል?

ሐ. ከ $\overline{\text{ጨደ}}$ እና ከ $\overline{\text{ጠየ}}$ የቱ ያንሳል?

መ. ከ $\overline{\text{ጠየ}}$ እና ከ $\overline{\text{ገቸ}}$ የቱ ይረዝማል?

ሠ. ከሁሉም ረዥሙ ውስን ቀጥታ መስመር የቱ ነው?

ረ. ሁሉንም ውስን ቀጥታ መስመሮች በማስመሪያ ለኩና አግኙ::

## 6.2 ጎነ አራት፣ ካሬ፣ ጎነ ሦስት እና ክብ ምስሎች

**ተግባር 6.3**


የሚከተሉትን የወለል ምስሎች ስም በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ::

1. 


ጎነ ________ ነው::

3. 

ጎነ ________ ነው::

2. 


________________ ነው::

4. 

አራቱም ጎኖች እኩል ናቸውን? ማስመሪያ ተጠቅማችሁ ለኩ::

5. በአካባቢያችሁ ወይም በቤታችሁ ከሚገኙት እቃዎች የትኞቹ ይመሳሰላሉ? እየዘረዘራችሁ ተወያዩባቸው?

6.



የሚመሳሰሉ ቅርፆችን አንድ አይነት በመቀባት ሦስት የተለያዩ ቀለሞችን ተጠቀሙ:: ለመምህራችሁ አሳዩ::


7. ርዝመቱ 4 ሳንቲ ሜትር ቁመቱ 3 ሳንቲ ሜትር የሆነ ጎነ አራት ምስል ሳሉ::

8. ርዝመቱ 6 ሳንቲ ሜትር የሆነ ጎነ ሦስት ምስል ሳሉ::


## 6.2.1 ጎነ ሦስት እና ጎነ አራት ምስሎች

1. ይህ ጎነ ሦስት ምስል ነው::
   - ጎነ ሦስት ፈከመ ተብሎ ይጠራል::
   - በአጭሩ ሲጻፍ △ፈከመ ይሆናል::

   △ የጎነ ሦስቱ መገለጫ ምልክት ነው::




ጎነ ሦስት ምስል





$\overline{\text{ፈመ}}$ ፣ $\overline{\text{መከ}}$ እና $\overline{\text{ፈከ}}$ የጎነ ሶስት ፈከመ ጎኖች ናቸው::

2. የተቀባው የጎነ ሦስት ፈከመ ወለል ነው::

ከላይ በጎነ ሦስት ምስል እንዳየነው የባለ ጎነ አራትንም ምሥል ባሕርይ እንመልከት::

ቀጥሎ ያለው ምስል የሚታየው ጎነ አራት በመባል ይጠራል::





ጎነ አራት ምስሎች በመለያያቸው ላይ በሚገኙ ነጥቦች ስያሜ ላይ በመመስረት ይሰየማሉ::

© MoE FDR Ethiopia Not to be republished

**ምሳሌ:-**

በውስን ቀጥታ መስመሮች መነ፣ ተቀ፣ መተ እና ነቀ የተሠራው ጎነ አራት **ቀነመተ** ተብሎ ይሠየማል::


1. ይህ ምስል ጎነ አራት **ተቀነመ** ተብሎ ይጠራል:: ጎነ አራቱ በሌሎች ስያሜዎች ሊጠራ ይችላል::




**ምሳሌ:-** ተቀነመ፣ መነቀተ፣ ነቀተመ በመባል መሠየም ወይም መጥራት ይቻላል::

- መነ፣ ነቀ፣ ቀተ እና ተመ የ'ተቀነመ' ጎኖች ናቸው::

## 6.2.2 ካሬ




በምስሉ የሚታየው አራቱም ጎኖቹ በርዝመት እኩል የሆነ ጎነ አራት ምስል ሲሆን **ካሬ** በመባል ይጠራል:: የተቀባው የጎነ አራት (ካሬ) **ሀለመሠ** **ወለል** ወይም **ጠለል** ነው::

**የቡድን ሥራ**


1. ርዝመቱ 3 ሳ.ሜ የሆነ ካሬ ሳሉ::
2. ርዝመቱ 5 ሳ.ሜ የሆነ ካሬ ሳሉ:: ዙሪያው ስንት ሳንቲ ሜትር ይሆናል?

## 6.2.3 ክብ

**ተግባር 6.4**

ተማሪዎች፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጋራ ተወያዩባቸው::

1. ከአካባቢያችሁ በሚገኝ እንደ ጣሳ፣ ሳንቲም፣ የልብስ ቁልፍ ወይም የክብ ቅርጽ ፈልጋችሁ በእርሳስ አክብቡ:: ምን አገኛችሁ? ለመምህራችሁ አሳዩ::




በክቡ ላይ የተመለከቱት ነጥቦች ዘ፣ ፈ፣ ጠ፣ የ፣ ነ እና መ ሌሎቹም ነጥቦች ከመሀል ነጥብ ‘ወ’ እኩል ርቀት ላይ ይገኛሉ፡፡

## መልመጃ- 6ሐ

. ጠ . የ . አ

.መ

. ዘ .ፈ .ነ

1. በነጥቦች ጠ እና የ የሚያልፍ ስንት ቀጥታ መስመሮች መሳል ይቻላል?
2. ነጥብ መ እና ነ በውስን ቀጥታ መስመር ስታገናኙ የሚፈጠረው ምን ይባላል?
3. ነጥቦች መ፣ነ እና አ በውስን ቀጥታ መስመሮች ስታገናኙ የምታገኙት (የሚፈጠረው) ምስል ምን ይባላል?
4. ነጥቦች ጠ፣የ፣ፈ፣ እና ዘ በውስን ቀጥታ መስመሮች ስታገናኙ የምታገኙት ምስል ምን ይባላል?
5. ነጥቦች የ፣ ፈ፣ ነ፣ እና አ በውስን ቀጥታ መስመሮች ስታገናኙ የምታገኙት ምስል ምን ይባላል?





6. የ $\overline{ሀለ}$ እና የ$\overline{ለሰ}$ መለያያ ነጥብ የትኛው ነው?
7. ጎነ ሦስት ምስል ሥሩ፡፡ መለያያዎቹን ጎኖቹን ሰይሙ፡፡ በምስሉ ላይ ወለሉን አመልክቱ፡፡
8. ጎነ አራት (ሬክታንግል) ምስል ሥሩ፡፡ መለያያዎቹንና ጎኖቹን ሰይሙ፡፡
9. ጎነ አራት (ካሬ) ምስል ሥሩ፡፡ መለያያዎቹን እና ጎኖቹን ሰይሙ፡፡
10. የክብ ምስል ሥሩና ሰይሙ፡፡ ወለሉን አሳዩ፡፡
11. በክብ መሳያ ከመሀሉ 2 ሳ.ሜ. ርቀት ያለው ክብ ሥሩ፡፡
12. ነጥብ ወን አመልክቱ፡፡ ወን መሀል በማድረግ በክብ መሳያ ክብ ሥሩ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished


## 6.3 በአካባቢያችን የሚገኙ ምስሎች (ቅርጾች)

**ተግባር 6.5**


የሚከተሉትን ምስሎች ስም ጥሩ።

ሀ. 


____________

ሐ. 


____________

ሠ. 

____________

ለ. 


____________

መ. 


____________

**ምሳሌ፡-**

የናፍጣ ወይም የዘይት መቅጃ ማንቆርቆሪያ ምን ቅርጽ አለው? ቅርጹ የክብና የክብ ክፋይ ውህድ ነው።




**ምሳሌ፡-**




© MoE, Not to be republished

# የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**1. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

ሀ. ጎነ ሦስት አራት መለያያ ነጥቦች አሉት።

ለ. ማንኛውም ጎነ አራት ካሬ መሆን ይችላል።

ሐ. ነጥብ መሠረታዊ የጂኦሜትሪ መነሻ ነው።

መ. ውስን ቀጥታ መስመሮች ቀጥታ መስመሮች መሆን ይችላሉ።

**2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።**

ሀ. ከሚከተሉት አንዱ አራት መለያያዎች አሉት።

ሀ. ክብ ለ. ጎነ ሦስት ሐ. ጎነ አራት

መ. ካሬ ሠ. ሐ እና መ

ለ. ከሚከተሉት አንዱ መለያያ ነጥብ የለውም።

ሀ. ጐነ-ሦስት ለ. ካሬ ሐ. ሬክታንግል መ. ክብ

ሐ. ውስን ቀጥታ መስመርን መሠየም የምንችለው በስንት ፊደል ነው?

ሀ. በአንድ ለ. በሁለት ሐ. በሦስት መ. በአራት

መ. የጥቁር ሰሌዳ ቅርጽ የሚመደበው በየትኛው ነው?

ሀ. ከጎነ ሦስት ለ. ከጎነ አራት ሐ. ከክብ

**3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።**

ሀ. ጎነ አራት ምስልን ለመስራት ስንት ውስን ቀጥታ መስመሮች ያስፈልጉናል?

ለ. ጎነ ሶስት ምስልን ለመስራት ስንት ውስን ቀጥታ መስመሮች ያስፈልጉናል?

ሐ. የዘይት መቅጃ ማንቆርቆሪያ የምንና የምን ቅርፅ ውህድ ነው?

መ. የሲሊንደር ቅርፅ የምንና የምን ውህድ ነው?

ሠ. አራቱም ጎኖች እኩል ርዝመት ያለው ጎነ አራት ምስል ምን ይባላል?

ረ. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ እቃዎች ጎነ አራት ቅርፅ ያላቸውን ዘርዝሩ።